

**መስታወት** እባላለሁ፤ የ17 አመት ልጅ ነኝ። የወደፊት ራዕዬ ዳኛ በመሆን የጾታ እኩልነትን ለማረጋገጥ መስራት ነው። ዳኛ የመሆን ፍላጎት እንዲያድርብኝ ያደረገው የመጀመሪያ አጋጣሚ ይህ ነው። ከዕለታት አንድ ቀን ጎረቤቴ ስታለቅስ እስካየሁበት ቀን ድረስ ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ምን እንደሆነ አላውቅም ነበር። ይቺን ጎረቤቴን በጣም ቅርብ የሆነ የቤተሰብ አባል እየደበደባት ነበር እና እሷ በጣም ፈራች። አንድ ቀን ብቻዋን በምትሆንበት ጊዜ ያ ለምን እንድሆነ ጠየኳት። እሷም በተደጋጋሚ እንደሚደበድባት እና ወሲባዊ ጥቃት እንደሚያደርስባት፣ ነገር ግን ምን ማድረግ እንዳለባት ግራ እንደገባት ነገረችኝ። እኔም ምን ማድረግ እንዳለብኝ ባላውቅም እሷን መርዳት እንዳለብኝ ግን አውቅ ነበር።

ስለሁኔታው ለእናቴ ነገርኳት፤ እሷም ፖሊስ ጠራች። ፖሊሶችም መጥተው ጥቃት አድራሹን ወሰዱት። ልጅቷም ይህን ስታይ እስከ ዛሬ ምንም ሳታደርግ በመቆየቷ በጣም አዘነች። ይህ ድርጊት ከዚህ በፊትም እንደነበረና ድርጊቱን ለማስቆም ምን ማድረግ እንደነበረባት ሳታውቅ ቆይታለች ።

አንድ ሰው ሌላውን ሰው ለምን እንደዚህ እንደሚጎዳ አልገባኝም ነበር። እናቴን ይህ ለምን እንደ ሆነ ጠየቅኳት ፣ እሷም ምክንያቱ አንዳንድ ሰዎች የሴቶችን እኩልነት ባለማክበር የሴቶች እና ልጃገረዶች ሰብዓዊ መብትን እንደሚጥሱ ነገረችኝ:::: ያ በእውነት ሞኝነት ነው። እናቴ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን ለማስወገድ የሚሰሩ ድርጅቶችን በመደገፍ መርዳት እንደምንችል ገለፀችልኝ። ገንዘብ ልንለግስ ወይም ጊዜያችንን በፈቃደኝነት ልንሰጥ እንችላለን፣ እና ለሌሎች ሰዎችም መርዳት እንዲችሉ ስለ ችግሩ መንገር እንችላለን።

ጀግና ለመሆን እና በፆታ ላይ የተመሰረተ ጥቃትን ለመዋጋት ወሰንኩ። ችግሩን በራሴ መፍታት እንደማልችል አውቃለሁ፤ ነገር ግን ሁላችንም ከተባበርን በአካባቢያችን ብሎም በሀገራችን እኔ እና እኔን መሠል እህቶቼን ከተለያዩ ፆታን መሠረት ካደረጉ ጥቃቶች መከላከል እና ጥቃት ሲደረስባቸውም ተገቢውን ድጋፍ እንዲያገኙ፣ ጥቃት አድራሾችም ተገቢው ፍርድ እንዲበየንባቸው መስራት እንችላለን። ይህም እንዲሆን እኔ፣ አንተ፣ አንቺ፣ እናንተ በጋራ መስራት ይጠበቅብናል !!!

# የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ

**አንቀጽ 576**
**ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን መጉዳት**

1. ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅን የሚጠብቅ ወይም በኃላፊነት የሚያሳድግ ማንም ሰው በማናቸውም ምክንያት ወይም ሁኔታ ልጁን የበደለ ፣ ችላ ያለ ፤ ከአቅሙ በላይ ያሰራ ወይም የመታ እንደሆነ ከሶስት ወር የማይበልጥ ቀላል እስራት ይቀጣል።

2. ወንጀሉ በልጁ ጤንነት፣ ደህንነት ወይም ትምህርት ወይም አካላዊ ወይም ስነልቦናዊ እድገት ላይ ከፍተኛ ጉዳት በሚያስከትልበት ጊዜ፣ አስፈላጊ ሲሆን ከቤተዘመድ ስልጣን የመሻር ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ ከአንድ አመት በማያንስ ቀላል እስራት ያስቀጣል።

3. ይህ ድንጋጌ ወላጆችን እና ተመሳሳይ ኃላፊነት ያላቸው ሌሎች ሰዎች ለመልካም አስተዳደግ የሚወስዱትን ሕግን የማይቃረን የዲሲፒሊን እርምጃን አይመለከትም /አንቅጽ 68/ ።

**አንቀጽ 620**
**አስገድዶ መድፈር**

1. ማንም ሰው የኃይል ድርጊት በመጠቀም ወይም በብርቱ ዛቻ ወይም ህሊናዋን እንድትስት ወይም በማናቸውም መንገድ መከላከል እንዳትችል በማድረግ ከጋብቻ ውጭ ከአንዲት ሴት ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት የፈጸመ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ያስቀጣል።

**2.** ወንጀሉ የተፈጸመው

**ሀ/** ዕድሜዋ አስራ ሶስት አመት ሆኖ አስራ ስምንት አመት ባልሞላት ሴት ልጅ ላይ ሲሆን፤ ወይም

**ለ/** በጥፋተኛው መሪነት፤ ቁጥጥር ወይም ስልጣን ስር በሆነ የመጦሪያ ቤት፣ የመማጠኛ በታ፣የሕክምና፣ የትምህርት፣ የጠባይ ማረሚያ፣ የመታሰሪያ ወይንም የተያዙ ሰዎች ማቆያ ተቋማት ውስጥ በምትገኝ ወይም በተከሳሹ ጥበቃ ወይም ቁጥጥር ስር በምትገኝ ወይም የእሱ ጥገኛ በሆነች ሴት ላይ ሲሆን፣ ወይም

**ሐ/** በእድሜ መግፋት፣ በአካል ወይም በአእምሮ ህመም፣ በመንፈስ ድክመት ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት የድርጊቱን ምንነት /ባህርይ/ ወይም ድርጊቱ የሚያስከትለው ውጤት ለይታ ለማወቅ ወይም ለመከላከል በማትችል ሴት ላይ ሲሆን ወይም

**መ/** በጭካኔ ወይም በማሰቃየት፣ ወይም ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆኑ ወንዶች ህብረት ሲሆን፤ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራት ይሆናል።

**3.** አስገድዶ መድፈሩ ከባድ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳትን ወይም ሞትን ያስከተለ ሲሆን ቅጣቱ የዕድሜ ልክ እስራት ይሆናል።

**4.** ከአስገድዶ መድፈሩ ወንጀል ጋር ተያይዞ ተበዳዩዋን ከህግ ውጭ ይዞ የማስቀመጥ ወይም የመጥለፍ ወንጀል የተደረገ ወይም ተበዳዩዋ በወንጀሉ ምክንያት በሽታ የተላለፈባት ሲሆን፣ አግባብነት ያላቸው የዚህ ህግ ድንጋጌዎች በተደራቢነት ተፈጻሚ ይሆናሉ።

**ማንኛውም አይነት ጾታዊ ጥቃት ሲያጋጥም በኢትዮጲያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር**

**ነጻ የስልክ መሰመር 7711**

**ላይ ደውሎ "0"ን በመጫን ነፃ የህግ ምክርና ድጋፍ አገልግሎትን በአማርኛ፣ በኦሮምኛና በትግርኛ ማግኘት ይቻላል።**

Supported by players of PEOPLE'S POSTCODE LOTTERY

Awarded funds from POSTCODE INTERNATIONAL TRUST

actionaid


## አክሽንኤይድ ኢትዮጵያ

ለሚኩራ ክፍለ ከተማ፣
ቀበሌ 13፣ የቤት ቁጥር 3044
1261, አዲስ አበባ, ኢትዮጵያ

ethiopia.actionaid.org
@ActionAidE
@ActionAid Ethiopia
Comms.Ethiopia@actionaid.org


# የሴቶች እና ልጃገረዶች ከጥቃት ነፃ ሆኖ የመኖር መብትን እናክብር፣ እናስከብር!

